# የስደተኞችና ስስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር

## የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አፈጻጸም

## መመሪያ ቁጥር 441/2013

## የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር

## የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አፈጻጸም

## መመሪያ ቁጥር 441/2013

1. መግቢያ

ሠራተኛው በሥራ ቦታው ላይ ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ እያለ የሚከሰት አደጋን አስመልክቶ ግልጽ የሆነ ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

ሠራተኛው የሚሰራበት አካባቢ፣ የስራ ፀባይ ወይም ቦታ በሠራተኛው ላይ የአካል ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ የማካካሻ ሥራ ለመሥራት ወጥነት ያለው አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

አስተዳደሩ የሚከተለውን ይህን የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር የሠራተኞች የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መመሪያ ቁጥር 441/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "የሕክምና ማስረጃ" ማለት በስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር የሥራ ሰዓትና ልዩ ልዩ ፈቃዶች መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2.5 መሰረት ይሆናል፡፡
2. "የሥራ ሁኔታ" ማለት በአስተዳደሩና በሠራተኛው መካከል ያለ ጠቅላላ የሥራ ግንኙነት ሲሆን፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነትን የሚመለከት ነው፡፡

3. *“የሥራ አካባቢ ደህንነት” (Occupational safety) ማለት አንድን ሠራተኛ በሥራ አካባቢ በሚገለገልባቸው የሥራ መሳሪያዎችና በሚከተላቸው የአሰራር ዘዴዎች ምክንያት ሊገጥሙት የሚችሉ አደጋዎችን የሚመለከት ነው፡፡*
4. *“የሥራ አካባቢ ጤንነት” (Occupational Health) ማለት ሠራተኛው ከሥራ አካባቢው ወይም ከተመደበበት የሥራ መደብ ባህሪ ሊመነጩ የሚችሉና በጤንነት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ሁኔታዎችን የሚመለከት ነው፡፡*
5. *“የሥራ አካባቢ ደህንነት እና ጤንነት” ( Occupation Safety & Health) ማለት ፡-*
    - *የሠራተኞችን አካላዊ፣ አዕምሮአዊ እና ማህበራዊ ደህንነታቸውን መንከባከብና ማሳደግ፣*
    - *በሥራቸው ምክንያት ጤንነታቸው እንዳይጓደል መጠበቅና መከላከል፣*
    - *ሠራተኞችን ከተፈጥሯዊ አካላቸው እና አእምሮአቸው ጋር በተጣጣመ መልኩ መድቦ ማሰራትና መከታተል ነው፡፡*
6. *“በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት” ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡*

    6.1 *“በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት” ማለት የአስተዳደሩ ሠራተኛ መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራው ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ሲሆን፣ የሚከተሉትን ይጨምራል፤*

*ሀ/ የአስተዳደሩ ሠራተኛ ከመደበኛ ሥራው ወይም መደበኛ የሥራ ቦታው ወይም ሰዓት ውጭ ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ሰው የተሰጠውን ትዕዛዝ በመፈፀም ላይ እያለ የደረሰን ጉዳት፣*

*ለ/ ሥልጣኑ በሚፈቅድለት ሰው የተሰጠው ትዕዛዝ ባይኖርም የአስተዳደሩ ሠራተኛ በመ/ቤቱ ውስጥ የደረሰን ድንገተኛ አደጋ ወይም ጥፋት ለመከላከል በሥራ ሰዓት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጭ በሚፈፀመው ተግባር ምክንያት የደረሰን ጉዳት፣*

*ሐ/ የአስተዳደሩ ሠራተኛ ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው ወደ ቤቱ በሚጓዝበት ጊዜ የደረሰን ጉዳት፣*

*መ/ የአስተዳደሩ ሠራተኛ ከሥራው ጋር በተያያዘ ግዴታ የተነሳ ከስራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ሥራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በሥራው ቦታ ወይም በመ/ቤቱ ግቢ ውስጥ በመገኘት የደረሰበትን ማንኛውንም ጉዳት፣*

*ሠ/ ሠራተኛው ሥራውን በማከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በአሰሪው ወይም በሶስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት፣*

*"በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" ማለት የአስተዳደሩ ሠራተኛ ከሚሰራው የስራ ዓይነት ወይም ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም፡፡*

*"የአካል ጉዳት" ማለት የመሥራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን በሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ነው፡፡*

## ***ክፍል ሁለት***

### ***3. የአካል ጉዳት መጠንና በሽታን የመወሰን ሂደት***

*ሠራተኛው ሆነ ብሎ በተለይም በመ/ቤቱ አስቀድሞ በግልጽ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች በመጣስ አካሉን ወይም አእምሮውን ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሰክሮ በሥራ ላይ በመገኘቱ የደረሰበት ጉዳት በሥራ ምክንያት እንደደረሰ ጉዳት አይቆጠርም፡፡*

### ***4. የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ መፈፀም የሚገባቸው ዋና ዋና ተግባራት***

### ***4.1 የአስተዳደሩ መ/ቤት፤***

*ሀ/ የሥራ ቦታው በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የማያስከትል መሆኑን የማረጋገጥ፣*

*ለ/ የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ለሠራተኞች የማቅረብና ስለአጠቃቀማቸው መመሪያ የመስጠት፣ ኃላፊነት አለበት፡፡*

*ሐ/ ከሥራ የሚመነጩ አደጋዎችና በሽታዎችን መከላከል፣ ስለመስሪያ ቤቱ ቅጥር ግቢ፣ ስለቢሮዎችና የስራ መሳሪያዎች እንዲሁም ሠራተኞች በሥራ ላይ እያሉ በሕይወትና ጤንነት ላይ ሊደርስ የሚችለውን ለከፍተኛ አደጋ የመጋለጥ የውስጥ ቁጥጥር ያደርጋል፡፡*

*መ/ በሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ዙሪያ ወቅታዊና የተሟሉ የመከላከያ መሳሪያዎችን ዓይነትና መጠን፣ በየጊዜው የተወሰዱ እርምጃዎችን የሚገልጹ መረጃዎችን እንዲሰበስቡ ያደርጋል፡፡*

*ሠ/ የተለየ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ነፍሰ ጡር ሴቶች፣ በሥራ ላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸውንና እንዲሁም ሌሎች የሥራ ባህሪይ ባስከተለው ሕመም የተጎዱ ሠራተኞችን በሐኪም የተረጋገጠ ማስረጃ ሲያቀርቡ ተገቢውን የሥራ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል፡፡*

*ረ/ አስተዳደሩ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት የመጠባበቂያና የመከላከያ ዘዴዎችን ያጠናል፣ የአስተዳደሩ ሠራተኞች ሥራ ላይ እንዲያውሉት ሥልጠና ስለሚሰጥበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ ለሥራው አስፈላጊውን በጀት ይይዛል፡፡*

### *4.2 ማንኛውም የአስተዳደሩ ሠራተኛ፡-*

*ሀ/ ደህንነትና ጤንነትን ለመጠበቅ የወጡ መመሪያዎችን የማክበር፣*

*ለ/ የተሰጡትን የአደጋ መከላከያ መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን በአግባቡ የመጠቀም፣*

*ሐ/ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲገምት ለሚመለከተው የመ/ቤቱ ኃላፊ ወዲያዉኑ የማሳወቅ፣*

*መ/ አስተዳደሩ በየጊዜው የሚያወጣቸውን የሥራ አካባቢ ደህንነት ጤንነት አጠባበቅ መመሪያዎችን የመከታተልና በሚሰጡ ሥልጠናዎች ላይም የመሳተፍ ግዴታ አለበት፡፡*

### *4.3 የአስተዳደር መ/ቤቱ የአስተዳደርና ፋይናንስ ማስተባበሪያ መምሪያ የሥራ ሂደት ተግባር፡-*

*ሀ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የቅርብ ክትትል የሚጠይቅ መሆኑን በመረዳት እንደዋና የሥራ ኃላፊነት በመውሰድ አመራር ይሰጣል፡፡*

*ለ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ባለሙያ አሰራሩን በየወቅቱ በመከታተልና በመገምገም የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወስድ ክትትል ያደርጋል፡፡*

*ሐ/ ለሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች መሟላታቸውን እና ሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡*

*መ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ መረጃ በመያዝ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይተገበራል፡፡*

*ሠ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን የተመለከቱ ጉዳዮች በባለሙያ ተጠንተው ሲቀርቡለት ውሳኔ ይሰጣል፡፡*

*ረ/ በሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ዙሪያ ከሠራተኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ወይም ጥቆማዎችን ተቀብሎ የማጣራቱን ተግባር እንዲያከናውን ለባለሙያ ይመራል፣ ከባለሙያ በሚቀርበው ሪፖርት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ ወይም እንዳስፈላጊነቱ ለበላይ ኃላፊ በማቅረብ ሲወስን እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡*

*ሰ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ሥራን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ከመ/ቤቱ ዓመታዊ የበጀት ፍላጎት ጋር በማቀድ ሥራ ላይ ያውላል፡፡*

*ሸ/ የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅን በተመለከተ አግባብ ካላቸው ሌሎች መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሥልጠና ዕቅድ እያዘጋጀ ሠራተኞች እንዲሰለጥኑ ያደርጋል፡፡*

## *5. የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠባበቂያና መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አጠናን ስልት*

### *የሰው ኃይል ልማት አስተዳደር ዶክሜንቴሽንና ኮሚኒኬሽን ቡድን፡-*

*ሀ/ የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ሲያጠና የሥራ መደቦች ዓይነት ብዛትና ሌሌችንም አግባብነት ያላቸውን መግለጫዎችና ፍሬ ነገሮች በቅድሚያ በማጣራት ይመዘግባል፡፡*

*ለ/ ሠራተኞች ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ እንደስራ ጠባይ ለሠራተኛው ደህንነት፣ ጤንነትና ንፅህና ሲባል መከላከያ መሳሪያዎቹና ቁሳቁሶች በእርግጥ ለሥራው ማስፈለጋቸውን ያረጋግጣል፡፡*

*ሐ/ ለሠራተኛ ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ የሚያገለግሉ መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ሊሰራ የሚችልበት ሁኔታ ካለ ያጣራል፡፡*

*መ/ ውስብስብ ወይም ግልጽ ያልሆኑ የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች ጥያቄ ሲቀርብ ሥራ በሚገኝበት አካባቢ በመገኘት የሚመለከታቸውን የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በማነጋገር አጥጋቢ ምላሽ ይሰጣል፡፡*

*ሠ/ የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት መጠበቂያና መከላከያ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶች አፈ,ቃቀድ ሂደት ውስጥ ለሥራና ለሠራተኛው ደህንነትና ጤንነት አጠባበቅ ጥንቃቄ ያደርል፡፡*

*ረ/ የሥራ ጉብኝት የሚደረግበትን የሥራ መደብ ተግባርና ኃላፊነት በማጥናት ሥራው የሚያስከትለው አደጋና የጤንነት ችግር መኖሩን ወይም አለመኖሩን ይረዳል፡፡*

*ሰ/ በጉብኝት ወቅት ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ይለያል፣ ሁኔታዎችን በአግባቡ ለመረዳት የሚያስችሉ መረጃዎችንም ያዘጋጃል፡፡*

*በ/ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎችና ሠራተኞች ጋር በመሆን የጉብኝቱን ዓላማ ይገልፃል፡፡*

*ተ/ ሥራው በሚከናወንበት አካባቢ በመገኘት ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ስለ ሥራው ይረዳል፡፡*

ቸ/ በቃለ መጠየቅ ወቅት ግልፅና ቀላል ቋንቋ ይጠቀማል፣ በጉብኝትና በቃለመጠየቅ ጊዜ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን እየመረጠ በማስታወሻ ይይዛል፡፡

ከ/ ባለሙያው ሪፖርት አጠናቅሮ የውሳኔ ሃሳብ በማዘጋጀት ለኃላፊው ያቀርባል፣ ኃላፊው በሚሰጠው ውሳኔ ወይም አስተያየት መሰረት እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡

6. ከሥራ በመጣ ጉዳት ምክንያት ስለሚሰጥ ሕክምናና ፈቃድ

6.1 በሥራው ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የአስተዳደሩ ሠራተኛ ለሚከተሉት የህክምና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን ወጪ አስተዳደሩን ይሸፍናል፡፡

ሀ/ በአገር ውስጥ የጠቅላላና የልዩ ሕክምና እንዲሁም የቀዶ ሕክምና ወጪዎችን፣

ለ/ የሆስፒታልና የመድሃኒት ወጪዎችን፣

ሐ/ የማንኛውም አስፈላጊ ሰው ሰራሽ ምትክ ወይም ተጨማሪ አካሎችና የአጥንት ጥገና ወጪዎችን፣

6.2 በሥራ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት የአስተዳደሩ ሠራተኛ ከጉዳቱ ድኖ ወደ ሥራው እስከሚመለስ ወይም በጉዳቱ ምክንያት ለዘለቄታ መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ማስረጃ እስከሚረጋገጥ ድረስ የህመም ፈቃድ ከሙሉ ደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡

6.3 ሠራተኛው ሕክምናውን በአግባቡ ባለመከታተሉ ወይም በሐኪም የተሰጠውን ትዕዛዝ ባለማክበሩ ሕክምናውን ያስተጓጎለ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 6.1 እና 6.2 መሰረት የሚሰጠው ሕክምናና ፈቃድ ይቋረጥበታል፡፡

## 7. ልዩ ትኩረት ስለሚሰጣቸው ሠራተኞች

የአስተዳደር መ/ቤቱ፡-

7.1 አንድ ነፍሰጡር ሠራተኛ ከእርግዝና በፊት ትሰራበት የነበረበት የነበረው የሥራ መደብ በጤንነቷ ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑ በሐኪም ከተረጋገጠ እስከምትወልድበት ጊዜ ድረስ ወደሌላ የስራ መደብ ተዛውራ እንድትሰራ ያደርጋል፡፡

*7.2 በሥራ ምክንያት በመጣ አደጋ የአካል ጉዳተኛ የሆነ የአስተዳደሩ ሠራተኛ ድጋሚ ጉዳት እንዳይደርስበት የሥራ አካባቢ ወይም ቢሮው በደህንነቱ ወይም በጤንነቱ ላይ አደጋ የሚያስከትልና ለእንቅስቃሴ ምቹ እንዲሆን ያደርጋል።*

## *8. ሶስተኛ ወገን ስለሚጠየቅ የካሳ ክፍያ*

*8.1 በሠራተኛው ላይ የደረሰው ጉዳት በሶስተኛ ወገን ጥፋት ምክንያት የደረሰ እንደሆነ አስተዳደሩ በጉዳት ምክንያት ለሠራኛው ባወጣው ወጪ መጠን ጉዳቱን ካደረሰው ወገን ካሳ የመጠየቅ መብት ይኖረዋል።*

*8.2 ሠራተኛው ጉዳቱን ካደረሰበት ወገን ካሳ የተቀበለ እንደሆነ አስተዳደሩ ያወጣውን ወጪ ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ ይቀንሳል። ሆኖም ሠራተኛው የተቀበለው የካሳ መጠን አስተዳደሩ ካወጣው ወጪ ያነሰ ከሆነ ልዩነቱን አስተዳደሩ ከሶስተኛው ወገን መጠየቅ ይችላል።*

## *9. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ*

*ይህ "የሥራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት" መመሪያ በዳይሬክተሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።*

*ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ*

*ዳይሬክተር*